በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

**ጠ/ሚር ጽቤት ርዕሰ አንቀጽ**
**መጋቢት 2013**

# ያለፉ ዓመታትን የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ስኬቶች በተሻሉ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች እና በጎ ስኬቶች ማስቀጠል

የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳ ተግባራዊ መደረግ ከጀመረ ከመስከረም ወር 2012 ወዲህ 18 ወራት ተቆጥረዋል። በነዚህ የትግበራ ወራት በቀደሙት ዓመታት ኢኮኖሚው ይመራበት ከነበረው የመንግስት ኢንቨስትመንት ተኮር ኢኮኖሚ ፖሊሲ ጉልህ የሆነ ሽግግር በማድረግ፤ የሀብት አመዳደቡ በገበያ መር መርህ ላይ እንዲመሰረት በማድረግና ለግሉ ዘርፍ ትኩረት በመስጠት፣ እና የተከሰተው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በኢኮኖሚው ላይ ያደረሰውን ተጽእኖ በመቋቋም በጠንካራ አቋም ላይ ይገኛል። እነዚህ ስኬቶች የተረጋገጡት የዓለም ኢኮኖሚ በቁልቁለት ጉዞ ላይ እያለና የሀገር ውስጥ ፖለቲካ በሁከት እየታመሰ ባለበት ወቅት ነው፡፡

ወደ ውድቀት የተቃረበውን የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ ለመታደግ በመንግስት የተወሰዱ ወሳኝ እርምጃዎች ባይኖሩ ወይም ተግባራዊ መደረግ የጀመሩት ጉልህ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች የኮቪድ ወረርሽኝ ባይከሰት ኖሮ ሊከሰት የሚችለውን ለውጥ መገመት አዳጋች ነው፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ሁኔታ በቅርበት ለሚከታተሉት ከ2008 ጀምሮ ከኢኮኖሚ ዕድገቱ፣ ከወጪ ንግድ፣ ከፋይናንስ ዘርፉ አለመረጋጋት ጋር በተያያዘ ኢኮኖሚው የሄደበትን የቁልቁለት ጉዞ ጠንቅቀን እናውቃለን።

**የኢኮኖሚ ማሻሻያው ተግባራዊ መሆን በጀመረበት የመጀመሪያ ዓመት መንግስት በወሰደው የተፋጠነ እና የተተቀናጀ የማክሮ-ፋይናንስ የማሻሻያ እርምጃዎች በመታገዝ ወደ ቀውስ እያመራ የነበረውን የማክሮ-ፋይናንስ ሁኔታ በቁጥጥር ስር በማዋል እና በቁልቁለት ጉዞ ውስጥ የነበረውን ኢኮኖሚ አቅጣጫ በመቀልበስ የኮቪድ-19 ያደረሰውን ጫና በመቋቋም የ6.1 በመቶ ዕድገት አስመዝቧል።** በውጭ ብድር እና ውጤታማ ባልሆኑ የመንግስት ኢንቨስትመንቶች ላይ ገደቦችን በመጣል ተስፋፊ የነበሩትን የፊሲካል እና የገንዘብ ፖሊሲዎች ጤናማ እንዲሆኑ ማድረግ የተቻለ ሲሆን፣ ጫናቸው ዝቅተኛ ከሆኑ ምንጮች የውጭ ሀብት በማሰባሰብ የውጭ ምንዛሬ ችግርን ለመቅረፍ ጥረት ተደርጓል፡፡ ጠቅላላ የመንግስት ዕዳ ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ያለውን ጥመርታ (debt to GDP ratio) ከ58 በመቶ ወደ 52 በመቶ ዝቅ ማድረግ የተቻለ ሲሆን፣ የኤክስፖርት አፈጻጸማችን መሻሻል እስከሚያሳይ ከውጭ የሚወሰዱ ጫናቸው ከፍተኛ የሆኑ የንግድ ብድሮች እንዲቆሙ እርምጃ ተወስዷል፡፡ በመሆኑም የንግድ ብድሮች ከአጠቃላይ የውጭ ብድር ፍሰት ውስጥ ያላቸው ድርሻ በ2010 ከነበረበት 50 በመቶ በ2012 ወደ 28 በመቶ ዝቅ በማለት የሀገሪቱን የብድር ጫና ስጋት በ2016 ወደ "መካከለኛ የስጋት ደረጃ" ዝቅ ለማድረግ የተያዘውን ግብ ለማሳካት በትክክለኛው መንገድ ላይ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶች መጠን ከአሥር ዓመታት የዝግመት አፈፃፀም እና ከ2008 ወዲህ ከያዘው የቁልቁሎሽ ጉዞ ተላቆ ዕድገት ማሳየት ጀምሯል (በ2012 በጀት ዓመት በ12 በመቶ አድጓል)።

**የኢኮኖሚ ማሻሻያው የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ ዘላቂነትን ለማረጋገጥና አዳዲስ የዕድገት አለኝታዎችን ለማመልከት መሠረታዊ ለውጦችን ያስተዋወቀ ነው፡፡** የኢኮኖሚ ፖሊሲያችን መሰረታዊ ግቦች ዕድገት፣ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ እና የሥራ ዕድል ፈጠራ ነበሩ። የማሻሻያ ዕቅዱ ለአካታችነት፣ የግሉን ዘርፍ አቅም ለመጠቀም፣ እና ተቀባይነት ያላቸውን የሥራ ዕድሎች (decent job) ለመፍጠር ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለ አሳይቷል፡፡ የኢንቨስትመንት እና የፋይናንስ ስትራቴጂያችን ከመንግስት ወደ የግል ኢንቨስትመንት እና ከዕዳ ወደ ድርሻ (equity) የፋይናንስ አማራጮች ጉልህ ሽግግር አድርጓል። የዚህ ለውጥ ዋና ዓላማ የመንግሥትን ኢንቨስትመንቶች መስፋፋት በመገደብ የግል ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ ምቹ የፖሊሲና የሪጉላቶሪ አካባቢን መፍጠር ነው።

በፋይናንስ ስትራቴጂው የተደረጉ ለውጦች እና ገበያ ተኮር የሃብት ክፍፍል እንዲኖር መደረጉ የማሻሻያው ወሳኝ የመጀመሪያ እርምጃ ተደርጎ ተወስዷል። ከዚህ አንጻር ጉልህ እርምጃዎች ተወስደዋል። ይበልጥ ውጤታማ ሊሆኑ ይችሉ የነበሩ የግሉ ዘርፍ ፕሮጀክቶችን በማሳደግ ፈንታ የመንግሥት ዘርፍ ፕሮጀክቶች በዝቅተኛ ወለድ ምጣኔ ፋይናንስ እንዲደረጉ ያስቻሉ ጨቋኝ የፋይናንስ እርምጃዎች እንዲቋረጡ ተደርገዋል። ከነዚህ ውስጥ አንዱና ዋነኛ የነበረው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከንግድ ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ ልማት ባንክ ገንዘብ እንዲዘዋወር ያስገድድ የነበረውና የ27% መመሪያ፣ ማሻሻያው ተግባራዊ መደረግ በጀመረ በሶስተኛው ወር በህዳር 2012 ተግባራዊነቱ እንዲቋረጥ ተደርጓል። አሁን መንግስት እንደገና ተጠናክሮ በተቋቋመው የግምጃ ቤት ሰነድ ሽያጭ ገበያ አማካኝነት ከግሉ ዘርፍ ጋር በገበያ ተወዳድሮ የፋይናንስ ፍላጎቱን የሚያሟላበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በመሆኑም የግሉ ዘርፍ የብድር አቅርቦት ከ2010 ጀምሮ በ80 በመቶ ዕድገት ያሳየ ሲሆን፣ የግሉ ዘርፍ ያገኘው ብድር ከአጠቃላይ ብድር ያለው ድርሻ በማሻሻያው ዘመን ወደ 64 በመቶ ከፍ ብሏል።

***ለኢንቨስትመንት እና ለንግድ ምቹ ፣ ግልፅ እና ተገማች የኢኮኖሚ ተቋማትን መፍጠር የማሻሻያው ዋነኛው ዓላማ ነው።*** መንግሥት ከጥቃቅንና አነስተኛ እስከ ድንበር ዘለል የሆኑ ኢንተርፕራይዞች ሁሉም አጋሮች የፈጠራ ሀሳቦቻቸውን እና ሀብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ ለማስቻል ምቹ የኢንቨስትመንት አካባቢ ሁኔታዎችን ለማሻሻል ቁርጠኛ ነው። ባለፈው በጀት ዓመት ከሀገሪቱ የፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የማይጣጣሙ የፖሊሲ እና የሕግ ማዕቀፎች እንዲለወጡ ተደርገዋል፡፡ ለንግድ እንቅስቃሴዎች አሳሪ የነበሩ ጠንካራ የኮርፖሬት አስተዳደር ልምዶችን ያራቆተው ከ1960ዎቹ ጀምሮ በሥራ ላይ የነበረው የዘውዳዊ ስርዓት የንግድ ህጋችን የግሉን ዘርፍ ተለዋዋጭ ፍላጎቶችን ለማሟላት ተሻሽሏል። አዲሱ የኢንቨስትመንት ህግ የሚፈቀዱትን የኢንቨስትመንት ዓይነቶች ከመዘርዘር ይልቅ የማይፈቀዱትን ወደ መዘርዘር ስልት የተሸጋገረ ሲሆን፣ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በበርካታ ዘርፎች መሰማራት እንዲችሉ የሚፈቅድ እና ለውጭ ባለሀብቶች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የማይፈቀዱትን የኢንቨስትመንት ዘርፎች ዝርዝር አመላክቷል፡፡ ወደ ቅይጥ ኢኮኖሚ የሚደረገውን ሽግግር ለመምራት በ1983 ሥራ ላይ የዋለው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚመሩበት ሕጋችን፣ የመንግስት ተቋማት የኢኮኖሚው ዋና ተዋናይ በማድረግ የግሉን ዘርፍ ሚና ያሳነሰና የገደበ ነበር። በለውጡ ማግስት የግሉ ዘርፍ ላይ በተደረገው ትኩረት መሠረት፣ ለመጽደቅ በረቂቅ ደረጃ ላይ የሚገኘው አዲሱ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሕግ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የኮርፖሬት አስተዳደር የግሉ ዘርፍ የሚመራበትን አስተዳደር እና አሰራር ሂደቶች የተከተለ እና ለውድድር ገለልተኛ መርህን የተከተለ እንዲሆን የሚያደርግ ሆኖ ተዘጋጅቷል። ከዚህ በላይ የተጠቀሱት እርምጃዎች በሀገሪቱ በኢንቨስትመንት ለተሰማሩ ባለሀብቶች የተሻሻለ አገልግሎት እንዲያገኙ ለማስቻል እና እየተስፋፋ ወዳለው የኢትዮጵያ ገበያ አዳዲስ ተቋማት እንዲመጡና ኢንቨስትመንት እንዲያካሄዱ ለመሳብ ያለሙ ናቸው።

በዚህ የሽግግር ወቅት አስተማማኝ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት ገበያ መር የሆነ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ብቻውን መፍትሔ ሊያመጣ እንደማይችል በአብዛኞቻችን ተመሳሳይ አረዳድ መኖሩ ግልጽ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የኢኮኖሚ ማሻሻያው ባለፉት አስር ዓመታት ውስጥ በነበረው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት አማካኝነት የተከሰቱትን የኢኮኖሚ መዛባቶች ለማስተካከል ያለመ ከመሆኑ ባሻገር አስቀድሞ በተነደፉ ሀሳቦች ላይ የተመሰረተ የኢኮኖሚ አብዮት ለማምጣት አለመሆኑን መረዳት ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም የኢኮኖሚ ዕድገቱን ቀጣይነት ከማረጋገጥ እና ማነቆዎችን ከመፍታት አንጻር አሁንም መንግስት በኢኮኖሚ ውስጥ የሚታዩ ክፍተቶችን ለማሟላት በትጋትና ግንባር ቀደም ሆኖ በልማቱ ይሳተፋል፡፡

***የመንግሥትና የግል ዘርፍ ተዋናዮች ከመቼውም ግዜ በላይ ወደ ብልጽግና የሚወስደውን መንገድ በጋራ ለመቅረጽ እየተንቀሳቀሱ ነው።*** በመንግስት የኢኮኖሚ ፖሊሲ አወጣጥ ላይ የሰላ ትችት እና ምክር ለመስጠት የሚያስችል ከፍተኛ የኢኮኖሚ አማካሪ ምክር ቤት ተቋቁሟል። በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራው የኢንቨስትመንት ቦርድም ከግሉ ዘርፍ አባላትን በውስጡ የያዘ ሲሆን መንግስት በሚሰጠው ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የግሉ ዘርፍ ድምፅ እንዲካተት ያስችላል።

በሀገራችን ባለፉት ጊዜያት ከዘይት እና ጋዝ እስከ ቱሪዝም፣ የፋይናንስ ቴክኖሎጂ፣ ማኑፋክቸሪንግ እንዲሁም እርሻ ድረስ ያሉት የኢንቨስትመንት አማራጮች በስፋት እና በዓይነት አድገዋል። በምስራቅ ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ጋዝ ከተገኘ ከ40 ዓመታት በኋላ ያልተነካው የኢትዮጵያ የነዳጅ እና ጋዝ ክምችት ወደ ገበያ ለመግባት ተዘጋጅቷል። ከቻይናው የፖሊ-ጂሲኤል ፔትሮሊየም ኢንቨስትመት ኩባንያ ጋር በተደረገው የጋዝ ንግድ ስምምነት መሠረት እስከ 6 ቢሊዮን ዶላር ገቢ የማስገኘት አቅም ያለው የተፈጥሮ ጋዝ በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት ውስጥ ወደ ውጭ መላክ እንደሚጀመር ይጠበቃል። በሀገሪቱ የመጀመሪያ የሆኑት የቱሉ ሞዬ እና ኮርቤቲ ጂኦ ተርማል የኢነርጂ ምንጭ ፕሮጀክቶች ሥራ በ800 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ኢንቨስትመንት በፈረንሳይ፣ በአሜሪካና አይስላንድ ባለሀብቶች ተጀምሯል፡፡

በገበያ የሚታየውን መሠረታዊ ክፍተት ለመሙላት የግሉ ዘርፍ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ በግብርና ዘርፍ የግብዓት እና የግብርና ምርትን ለገበያ ተደራሽ ለማድረግ የግሉ ዘርፍ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ ባለፈው ሳምንት የግብርና ሚኒስቴር ከአንድ የግል አየር መንገድ ኢንተርፕራይዝ ጋር የአንበጣ መንጋ ወረርሽን ለመከላከል የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርሟል፡፡

መንግስት ግንባር ቀደምነቱን በመውሰድ የሀገሪቱን የቱሪዝም አቅም አሟጦ ለመጠቀም በአዲስ አበባ በሚገኙ አዳዲስ ፓርኮች ውስጥ እንደሚታየው እየሰራ ነው። አንድነት፣ እንጦጦ እና ሸገር ፓርኮች - የሀገሪቱን ታሪካዊ፣ ባህላዊ እና ሥነ-ምህዳራዊ መስህቦች የሚያሳዩ ማራኪ ስፍራዎች ናቸው። እነዚህ የግል እና የመንግሥት ኢንቨስትመንቶች መንግሥት በአዳዲስ የኢኮኖሚ ዘርፎች ውስጥ ያለውን እምቅ አቅም ለመክፈት ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳዩ ናቸው።

**ግልጸኝነትን የተላበሱ እና ገበያ ተኮር በሆኑ የኢኮኖሚ ተቋማት እና ጠንካራ የፖለቲካ ቁርጠኝነት በመታገዝ ተግባራዊ እየተደረገ ያለውን ማሻሻያ በመጠቀም ከፍተኛ ተስፋ የተጣለባቸው ዕምቅና ያልተነኩ ዕድሎቻችን በማሻሻያው ዘመን መጨረሻ ወደ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ሽግሽግ እንደሚወስዱን ይጠበቃል፡፡** በያዝነው የበጀት ዓመት መጨረሻ እንደሚቋቋም የሚጠበቀው የካፒታል ገበያ በኢኮኖሚው ውስጥ ተጨማሪ የፋይናንስ ምንጮችን ያስተዋውቃል ተብሎ ይጠበቃል። የካፒታል ገበያው ከዕዳ ወደ ድርሻ (equity) የፋይናንስ አማራጮች የመሸጋገር ዕቅዳችንን ያረጋግጣል። የመንግስት የልማት ድርጅቶችም ሆኑ የግል ኩባንያዎች የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶችን ለመሳብ የሚያስችላቸው ይሆናል። በእንደ ቴሌኮም እና ሎጅስቲክስ ባሉ ዘርፎች ለኢንቨስትመንት ክፍት ለማድረግ የተጀመረው ርምጃ እንዲሁም የንግድ ሥራን ለማቀላጠፍ የሚደረገው ማሻሻያ የኢኮኖሚውን ተወዳዳሪነት እንዲጨምር እና ተጨማሪ የኢንቨስትመንት ዕድሎች እንዲከፈቱ የሚያደርግ ነው። የዓለም ንግድ ድርጅትን ለመቀላቀል የሚካሄደውን ድርድር በፍጥነት ማጠናቀቅ እና የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣናን መቀላቀል በሕግ ላይ የተመሠረተ የግብይት ሥርዓት እንዲኖር አስተዋፅዖ ያደርጋሉ። እንዲሁም የገበያዎችን ተደራሽነት ያሻሽላሉ።

**የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳው በጠንካራ የግል ዘርፍ፣ ግልጽና ተገማች በሆነ ፖሊሲና ሪጉላቶሪ ማዕቀፍ መንግስትን በመምራት ያልተነኩና ያልተዳሰሱ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጮችን በቁርጠኝነት በመጠቀም ጥልቅ የኢኮኖሚ ልማትን ማረጋገጥ ነው፡፡** በማሻሻያው የትግበራ አጋማሽ የተመዘገቡ ስኬቶች የማሻሻያ እርምጃዎቹ የማክሮ ኢኮኖሚው በተረጋጋ ጎዳና ላይ እንዲጓዝ፣ ጎልተው የሚታዩ አዳዲስ እምቅ አቅሞች እንዲወጡ፣ እንዲሁም የግሉ ዘርፍ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አቅም ላይ እምነቱ እንዲጨምር አድርጓል። የማሻሻያው ትግበራ ውጤቶች ያለፉትን ስኬቶች ለማስቀጠልና የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ሽግግር በመምራት ለአስር ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ ዝግጅት መሰረት ጥሏል።

//